*የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ*
*ሪፐብሊክ ኤምባሲ ብራስልስ*

*Embassy of the Federal Democratic*
*Republic of Ethiopia Brussels*

Ref: BE/POL/M/PD/5/33/06

ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ.ም.

ለቃል-አቀባይ ጽ/ቤት

ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

አዲስ አበባ

ጉዳይ:- በቤልጀምና ሉግዘምበርግ ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ጋር የተካሄደውን ስብሰባ ይመለከታል::

እ.ኤ.አ. ህዳር 28 ቀን ቀን 2006 ዓ.ም. በብራሰልስ የኢፌዲሪ ኤምባሲ ከ250 በላይ ከሚሆኑ በቤልጀምና ሉግዘምበርግ ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ጋር በሀገራችን ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በብራልስ ከተማ ውይይት አካሄደ:: በዕለቱ በቤኔሉክስ ሀገራትና በአውሮፓ ህብረት የኢፌዲሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ንግግር ያደረጉ ሲሆን፣ አምባሳደሩ በንግግራቸው ሀገራችን ባለፉት ዓመታት በኢኮኖሚውና ማህበራዊ መስክ ያስመዛጋበችውን ተከታታይ ዕድገት በማውሳት፣ የዕድገትና ትርንስፎርሜሽን ዕቅዱ ከማሳንት አንጻር መንግስት ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ጨምሮ ሌሎች ታላላቅ ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት ለማጠናቀቅ በትጋት እየሰራ መሆኑን አብራርተዋል::

ስለሆነም መንግስት በሀገራችን እየተካሄደ ባለው መሰረት ሰፊ የልማትና የህዳሴ ጉዞ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ ግልፅ የዲያስፖራ ፖሊሲና ስትራቴጂ በማውጣትና ራሱን የቻለ አደረጃጀት በመፍጠር እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ገልፀዋል:: አምባሳደሩ አክለውም በዲኘሎማሲ መስክ ሀገራችን ያመዘገበች ያለውን ስኬት በማንሳት፣በዘርፉ ከዳያስፖራው ጋር የሚኖረን ሥራ እንድ አንድ ስትራተጂያዊ ግብ የተወሰደ ሲሆን፣ የፍላጐት፤ የጥቅምና የሃሳብ የአመለካከት ልዩነቶች መኖር የነበረ፤ ያለና ወደፊትም የሚኖር ሲሆን ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በቅድሚያ የዳያስፖራው መብቶችና ጥቅሞች የሚከበሩበት፤ የዳያስፖራ አባላት በሀገሪቱ እየተካሄደ በሚገኘው ሰፊ የማሕበራዊና ኢኮኖሚ በአጠቃላይ የትራንስፎርሜሽን ጉዞ ተሳትፎና ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል ቀዳሚው ሥራችን ነው በማለት አብራርተዋል::

ከዚህ ጋር በተያያዘ መንግስት በቅርቡ ዲያስፖራውን የቤት ልማት ፕሮግራም ተጠቃሚ ለማድረግ ባወጣው ዕቅድ መሰረት በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች አስፈላጊውን ዝግጅት በማጠናቀቅ በቅርቡ ምዝገባ እንደሚያካሄድ ገልፀዋል:: የሳውዲ መንግስት በዜጎቻችን ላይ የተፈፀመውን ኢ-ሰበአዊ አያያዝ በከፍተኛ ሁኔታ የሚወገዝ ሲሆን፣

በዜጎቻችን ላይ በሀገሪቱ የፀጥታ ሀይሎች ተከሰተው የሰበአዊ መብት ጥሰትና ለ3 ዜጎቻችን ግድያ አስፈላጊውን ማብራሪያ በመጠየቅ በቀጣይ ለሚወሰደው ዲፕሎማሲያዊ እርምጃ መንግስት ዝግጅት የተደረገ ሲሆን፣ ነገር ግን በችግር ላይ ያሉ ዜጎቻችን በማጓጓዝ ቅድሚያ መስጠት አለብን በማለት ዜጎችን በመመለስና ወደ ማህረሰቡ በማቀላቀል በመንግስት በኩል ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ነው በማለት አብራርተዋል::

በመጨረሻም ዲያስፖራው ሚሲዮኒ እየሰጠው በሚገኘው የቆንሰላና የቪዛ አገልግሎት እንዲሁም በሀገር ውስጥ የተካሄደ ባለው የመልካም አስተዳደር ግንባታ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣ሀገራችን ድህነትን ታሪክ ለማድረግ እያስመዘገበችው በምትገኘው የልማት እንቅስሰቃሴ ዲያስፖራው ከአሁን በፊት ሲያደርገው እንደቆየው ሁሉ ሪሚታንስ በመላክ፣ በእውቀት ሽግግር፣ ኢንቨስት በማድረግ፣ የሀገራችን የቱሪዝም ሀብት በማስተዋወቅና በሀገር ገፅታ ግንባታ ላይ ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ በሀገሩ ልማት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪ አቅርበዋል::

በዕለቱ ከስብሰባው ከተሳታፊዎች በታላቁ የህዳሴ ግድብ የዓለም አቀፉ ኤክስፐርቶች ቡድን ሪፖርት ተግባራዊነት፣ በሳውዲ ዜጎቻችን ላይ የደረሰው ኢ-ሰበአዊ አያያዝ እና በቤት ልማት ዙሪያ መንግስት እየወሰደ በሚገኘው እርምጃዎች ላይ ጥያቄዎች የተነሱ ሲሆን፣ ክቡር አምባሳር ተሾመ ቶጋ በተነሱት ጥያቄዎች ላይ መንግስት እየወሰዳቸው ያሉትን እርምጃወዎች ገልፀዋል:: በመሆኑም በርካታ የዲያስፖራ አባላት መንግስት በሀገራችን ልማትን ለማሳካት እያደረገው ያለው ጥረት በሚበረታታ መሆኑን በመግለፅ፣ የታላቁ ህዳሴ ግድብን ጨምሮ በሀገራችን እየተካሄደ በሚገኘው ከፍተኛ የመሰረተ ልማት ስራዎች ላይ ያላቸውን አድናቆት በመግለፅ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል::

በመሆኑም በዕለቱ በቤልጀምና ሉግዘምበርግ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የሚውል የ3410 ዮሮ የቦንድና የደረት ፒን ግዥ ያካሄዱ ሲሆን፣ የዲያስፖራ አባላቱ በቀጣይ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሁለንተናዊ ድጋፋቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ አረጋግጠዋል::